# በአንድነታችንና በሰላም ለመኖር
# ወደ 1966 ክልላችን መመለሱ ይመረጣል
(ብርሃነ ደስታ ኃይለየስ)

የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) መሪዎች ገና በትግል ላይ ጫካ እያሉ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመከፋፈል ባቀዱት መሰረት፣ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ብሔር/ብሔረሰቦች መብት ይከበር በ ሚል ሳቢያ አገሪቷን በክልል ሸንሽነው የፌዴራል መንግሥት ለማቋቋም መስማማታቸው እሙን ነ ው። የስምምነቱም ሰነድ "የተሰኔ ማኒፌስቶ" ተብሎ እንደሚጠራና ይኅንኑ ማኒፌስቶ በሥራ ላይ ለ ማዋል፣ ወያኔ ስልጣን ከያዘ በኋላ የአሻንጉሊት ፓርላማ አቋቁሞ በቻርተሩ ላይ እንዲሰፍር አስደርጓ ል። ቻርተሩንም የኢትዮጵያ ሕዝብ እውቅና እንዲሰጥና እንዲያከብርለት አስታውቋል። ሆኖም የአ ትትዮጵያ ሕዝብ ግልጽና ዲሞክራሳዊ በሆነ መንገድ ስለአስተሳተፈበት ሕገ መንግሥቱ ሊጸና አይገ ባውም በማለት በሰላማዊ መንግድ ትግሉን እንደቀጠለ ይገኛል። ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ወያኔ የ ሚጠቀምባቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስመሳይ ዘዴዎች "ሴልፍ ዲተርሚነሽን" የሚለው የተባ በሩት መንግሥታት ቻርተርና፣ የኮሚኒስቱ "ሴልፍ ዲተርሚነሽን አፐቱ ሴሴሽን (እስከ መገንጠል)" የሚለው መርሆ ነው። በመሰረቱ እነዚህ መርሆዎች በማነኛውም መለኪያ በአንድነቷ ፀንታ ለኖረ ች ኢትዮጵያን በመሰልች ጥንታዊት አገር ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም። ስለዚህ ሕዝቡ በሰ ላምና በፍቅር ተከባብሮ ወደ ኖረበትና እንዲሁም በሰላምና በፍቅር እንዲኖር ከተፈለገ፣ በጎሳና በቋን ቋ መከፋፈሉ ቀርቶ ወደ ቀድሞው 1966 ዓ.ም. ወደ ነበረው ድንበራችን መመለሱ እጅግ ተመራጭ ነው። ሆኖም የብሔሮች መብት መከበር አለበት በሚል ሰበብ የግድ ሕዝቡ በጎሳና በቋንቋ መከፋፈ ል አለበት ከተባለ ደግሞ፣ ከመሐምድ ግራኝና ከኦሮሞ ወረራ በፊት ወደአለው ይዞታችን መመለስ ይኖርብናል።

ሁላችንም ከታሪክ እንደምንረዳው፣ ኢትዮጵያ የብዙ ዘመን የነጻነት እድሜ ያላትና ጥንታዊ ከ ሚባሉት ጥቂት ሐገሮች አንዷ መሆኗ አያሌ የታሪክ መጻሕፍቶችና እንዲሁም ስሟ በመጽሐፍ ቅ ዱስ ተደጋግሞ መጠቀሱ ግዙፍ ምስክር ነው። ታሪክም እንደሚነግረን ከሆነ የአገሪቱ የካርታ ስፋት በየጊዜው እያነሰና እየጠበበ ሄደ እንጂ፣ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደሚተርኩት በኮሎኒ ያስ ፋፉችው የግዛት ይዞታ አይደለም። ጥንታዊት ኢትዮጵያ ዛሬ ከምናያት መልክአ ምድር እጅግ በጣ ም የሰፋች፣ በደቡብና ደቡብ-ምስራቅ፣ የምስራቅ-አፍሪካ ማህበረ-ሰብና ማዳጋስካርን አካቶ በምሥራ ቅ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ እስከ የመን፣ እንዲሁም ዘይላ፣ ታጁራንና አርጌሳን ተራምዶ፣ ሕንድ ውቅያ ኖስን የሚያካልል፣ በምእራብ ሰሜን ኑብያንና ስናርን በማጠቃለል ደቡባዊ ግብጽ ድረስ የሚሸፍን የ ካርታ ስፋት እንደነበራት እነሄሮድተስ መስክረውላታል፣ በቅርቡም ዘመን እንኳን (1270-1800 Ric hard Pankhurst: The Ethiopian Borderlands, Dr. Sergew Hable-Selassie, The Ancient Medieval History of Ethiopia) በተባሉት መጻሕፍት እንደሚያ መለክቱት፣ ከይኩኖ አምላክ እስከ ሱስንዮስ በነበረው ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ድንበር በአራቱም ማእዘን አሁን ካለው የመሬት ካርታ እጅ ግ በጣም ይሰፋ እንደነበረ ይነግሩናል፣ አጼ ዘርአያዕቆብ፣ አጼ እስክንድር፣ አጼ ሠርጸድንግል፣ አጼ አምደጽዮን በነገሱበት ዘመን እንኳ የዘይላና የቦኮ ወደብ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደነብረች እን ዲሁም ከላይ የተጠቀሱትና (የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ - ከኑቢያ እስከ ይኩኖ አ ምላክ፣ እንዲሁም ከይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ቲዎድሮስ በክቡርአቶ ተክለጻድቅ መኩሪያ ) መጻሕፍ ቶች ላይ ይሄንኑ ያረጋግጡልናል። ይህ ለማይሙና ያህል ተጠቀሰ እንጂ ስለ ኢትዮጵያ መልክአ ምድር ወይም የካርታ ስፋት በየዚዜው እያነሰና እየጠበበ የመጣበትን ምክንያት ጭምር በሰፊው የ ሚገልጹ ሌላ ብዙ መጻሕፍቶች አሉ፣ ዋና ዋና ምክንያቶቹም በዘመኑ የነበሩ መሪዎች ተደጋጋሚ ጦ ርነቶች በመከሰታቸው ምክንያት ድክመትና ከውጪ ወራሪዎች ጋር በሚደረገው ጦርነት ተመጣጣ

ኝ ባልሆነ የጦርመሳሪያ እንደሆነ ያሰምሩበታል። ሆኖም  ሁልጊዜም ቢሆን፣ መልከአ ምድሯ ሰፋም
ጠበበ፣ ኢትዮጵያ አህጳዊ አካልና አህጳዊ መንግሥት የነበራት እንጂ ሶቪየት ዩኒየን (SovietUnion)
ንደነበረው ከብዙ  አገር ጋር ከጊዜ በኋላ የተገጣጠመች ወይም የተዋዋሀደች አገር አልነበረችም አይ
ደለችምም።

እርግጥ በዚህ 3ሺ ዘመን የፖለቲካ ስብጥርና በውጪ ኃይል ጣልቃ ገብነት ምክንያት ለጥቂ
ት ዘመናት የመሳፍንቶች መከፋፈል ስለተከሰተ አህጳዊው መንግሥት ተንሳፎ የመሳፍንታዊ እራስ
ገዝ ፌዴራላዊ መንግሥት መሰል ተከስቶ እንደነብር ይታመናል፣ ሆኖም እንደ ክፍለ ሐገር  አስተዳ
ዳሪ ሆነው መሳፍንቱ ሲያስተዳድሩ ኖሩ እንጂ፡ ተግንጥለው የራሳቸውን ሉአላዊነት ያገኙበት ጊዜ አ
ልነበረም። ሁሉም በአንድ ሉአላዊ ኢትዮጵያ ስር ነበር የሚተዳደሩት።

ምንም እንኳን ይህ የተፈጠረው ክፍፍል በዘመኑ የኢትዮጵያን አንድነት ባያናጋም ከጊዜ
ብዛት ለውጭ ጠላቶች መግቢያና ማጥቂያ ምቹ ሆኖ ስለታያቸው፣ ይህንን ስርአት ደጋፊዎች የሆኑ
ቱን ጥቂቶች መሳፍንቶች በመደምሰስ፣ አጼ ቲዎድሮስ  ወደ ጥንቱ አህጳዊ መንግሥት መልሰውታ
ል። ይህም የመሳፍንቶች መከፋፈል በዘመኑ በሕዝብ ያልተደገፈ በመሆኑ ከመሳፍንቶቹ በስተቀር አ
ጼ ቲዎድሮስ በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ብዙም ተቃውሞ አልነበረም። ድርጊታቸውንም ሕዝብና ታ
ሪክ እስካሁን ሲያወድሳቸው ይኖራል። ወያኔም ለራሱ የፖለቲካ ጥቅም  ይሁን ወይም አምኖበት ባ
ይታወቅም፣ ወደ አዲስ አበባ ያመራውን የጦር ግንባር "የቲዎድሮስ ዘመቻ" ብሎ ነው የሰየመው።
ሆኖም "ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልም" እንደተባለው ሁሉ ወያኔ በተቃራኒው ሀገርን የሚ
ከፋፍልና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚያፈርስ ሕገ መንግሥት ስልጣን በያዘ ጥቂት ቀናቶች  ውስ
ጥ አርቅቆ አጸደቀ እንጂ የአጼ ቲዎድሮስን አስተሳሰብ አልተከተለም። ስለዚህ የደርግ መንግሥት
እስከወደቀበት ጊዜ ድረስ፣ ኢትዮጵያ ስትተዳደርበት የነበረው ሕገመንግሥትና መርሆ አንድ አገር፣
አንድ ሕዝብ፣ አንድ ድንበር፣ አንድ መንግሥት እንደነበርና፡ እኛም በዕድሜያችን ደርሰን በአካል
ያየነው ሀቅ ነው።

የሕዝቡም አሰፋፈር ተመሳጥሮ ሲሆን አገሪቱም ለአስተዳደር ምቹ እንዲሆን ብቻ በአውራ
ጃና በወረዳ ተከፋፈለች እንጂ በጎሳ አንድም ጊዜ ተከፋፍላ አታውቅም። ለምሳሌ ያህል በአጼ ኃይለ
ሥላሴ ጊዜ ለአስተዳደር ምቹ እንዲሆን በ14 ጠቅላይ ግዝት ስትከፈል እያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ደ
ግሞ በብዙ አውራጃና ወረዳዎች ተከፋፍሎ ነበር። በደርግ ጊዜም ቢሆን የነበረውን ስርአት ሳይቀይ
ር የስም ለውጥ ብቻ "ክፍለ ሐገር" በማለት ሰይሞት ነበር። የደርግ ስርአት ወደማለቂያው ሲደርስ
በበለጠ ለአስተዳደር ምቹ ይሆን ዘንድ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅ በማለት የነበሩትን ክፍለ
ሐገሮች ከፋፍሎአቸው ነበር። ይሁን እንጂ  በማናቸውም ጊዜ እነኚህ ጠቅላይ ግዝቶች ወይም ክፍለ
ሐገሮች በቋንቋና በጎሳ ተከልለው የዚህ ወይም የዚያ ብሔረሰብ ክልል ተብለው ሲስተዳደሩ አልነበ
ርም። ባለፈው የአጼዎች ዘመነ መንግሥት መሬት የግል ሲሆን እያንዳንዱ ግለሰብ በሰፈረበት ወረዳ
የጎሳ ልዩነት ሳያግደው በኢትዮጵያዊነቱ የመሬት ንብረት የመያዝና የማልማት መብት ነበረው። በ
ደርግ ጊዜ መሬት የሕዝብ ስለነብረ በገበሬ ማህበር ተደራጅቶ የጎሳ ልዩነት ሳያግደው በኢትዮጵያዊ
ነቱ ንብረት የመያዝና የማፍራት መብቱ ተከብሮ ይኖር ነበረ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ዘመነ መንግሥታት  ሕዝቡ ተመሳጥሮ በወንድማማችነት አብሮ ተ
ፋቅሮና ተጋብቶ ይኖር ነበር፣ ቅሬታና በደል ቢደርስበትም ከመንግሥት ፍትሕ ባለማግኘቱ እንጂ
አንዱ ጎሳ ሌላውን በደለኝ በማለት አልነበረም፡ በዚህም ምክንያት ነው፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ  በጎሳና
በቋንቋ ሳይከፋፈል መሬት ላራሹ እንዲሰጥ፣ ፍርድ እንዲስትካከል፣ አብዮቱን አቀጣጥሎ የነበርውን

የዘውድ መንግሥት እንዲወድቅና ሌላ የተሻለ ስርአት እንዲተካ የጣረው:: የብሔሮችም ጥያቄ የመ ጣው የሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለም በመከተል ከተራማጅ ምሁራንና የፖለቲካ ድርጅቶች ነው እንጂ ከሕዝብ የመጣ ጥያቄ አልነበረም: የሕዝብ ጥያቄ ጭሰኝነት እንዲቀር የመሬት ስሪትና ድልድል እን ዲኖር እንዲሁም ስለዳኝነት ፍትሕ ትኩረት እንዲሰጠው ነበረ:: ተራማጁ ግን የሕዝቡን ጥያቄ ትኩረ ትና ክብደት ሳይሰጠው በራሱ ውሳኔ እኔ አውቅልሀለሁ በማለት የአብዮቱን አቅጣጫ በራሱ ግብታዊ መርሆ ስለመራው፣ ደሀው ገበሬ በርስትነት ይዞ የነበረውን እርቦ መሬት አስወሰደበት እንጂ የጠየቀ ውን የመሬት ድልድል ድርሻ አላገኘም:: ፍትሕንም በሚመለከት አምባ ገነን ግለሰቦችና ካዲሬዎች በቤተሰቡና በልጆቹ ላይ በማን አለብኝ የግፍ እስራትና የሞት ፍርድ አደረሱበት እንጂ የተመኘውን የፍርድ መስተካከል አላገኘም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ለ17 ዓመታት እየማቀቀና እያዘነ ሳለ ይባስ ብሎ "በእንቅርት ላ ይ ጆሮ ደግፍ" እንደተባለው ሐገርና ሕዝብን የሚከፋፍል የወያኔ ቡድን መጣበት:: የደርግ መንግስ ት ወድቆ ኢሕድግ/ወያኔ በ1983 ዓ. ም የመንግሥቱን ስልጣን ሲይዝ የሽግግር መንግሥት አቋቁሞ: ወደዚያው ምንም ጊዜ ሳይወስድበት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ሳይጠይቅ የሕዝቡን ስ ልጣን በመጋፋት ሁለት ዓቢይ ውሳኔዎችን አሳለፈ::

> አንደኛ ቀድሞ የነበረውን አህዳዊ መንግሥት አፍርሶ የብሔር ብሔረሰቦች መንግሥታት እንዲቋቋሙና ራሳቸውን ችለው እንደአንድ መንግሥት እንዲ ያስተዳድሩ፣ ከዚያም ባሻገር ተደራጅተው ከፈልጉ የራሳቸውን እድል እስከ መገንጠል ለመወሰን የሚያስችል መብት ሰጠ፣ ይህም ማለት የዛሬዋ ኢትዮ ጵያ ከአኩሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ለ3000 ዘመናት የኖረችው ኢትዮጵ ያ ሳትሆን በዘጠኙ ብሔሮች ካውንስል ስምምነት የተፈጠረች አዲስ ኢትዮጵ ያ ናት፣ ለማለት ያስደፍራል::
>
> ሁለተኛው ውሳኔ ደግሞ፣ ቀድሞውንም ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል በትጥቅ የታገለ በመሆኑ ስልጣን እንደያዘ ስልጣኑን በመጠቀም ኤርትራ ተገ ንጥላ ነጻ እንድትወጣ ፈቀደ፣ከዚያም ለተባበሩት መግሥታት በጽሑፍ አቅርቦ በሰኩሪቲ ካውንስል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ እንድትሄድ እውቅና እንድ ታገኝ ተማጽኖ አስወሰነ:: በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ አካሏን፣ ኤርትራን፣ ከ ማጣቷም ባሻገር፣ ታሪካዊ ጠላቶቹዋ አመቺ ጊዜ እየመረጡ ድንበሯን ጥሰው እየገቡ የሚያጠቁበትን፣ ኢትዮጵያ ሌት ተቀን በተጠንቀቅ ቆማ የምትጠባበ ቅበትን በር፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ አውታር የሆነውን የባሕር ወደቦቿን እን ድትነጠቅ አስደረገ:: በጠቅላላው የሰኩሪቲ በሯንና የኢኮኖሚ አውታር ወደቦ ቿን አስወሰደባት::

ይሄንንም ድርጊት የሕዝብ ውሳኔ ለማስመሰል እራሱ የፈጠራቸውንና መሰሎቹን አሰባስቦ የ አሻንጉሊት ፓርለማ አቋቁሞ ውሳኔው በሕገ መንግሥት ጸድቋል በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያ ውቅለትና እንዲያከብርለት አስታውቀ፣ በመጀምሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ ዳር ድንበርና ሉዐላዊነቷ በ ምንም መልኩ ለድርድር ወይም ለሕዝብ ተወካዮች ውሳኔ መቅረብ የለበትም ነብር:: ሆኖም ግልጽ በ ሆነ እውነኛ የዲሞክራሲን ስርአት በተከተለ መልክ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፓርለማው ምርጫ ያልተ ካፈለ በመሆኑ፣እንዲሁም ሕገ መንግሥቱ የሕዝቡን ጥያቄና ፍላጎት የማያካትት ስለሆነ፣ እስካሁን ያ ላቋረጠ ተቃውሞ ገጥሞታል:: በዚህም ምክንያት በየጊዜው በሚነሳበት ተቃውሞ ሕገ መንግሥቱን

አላከበራችሁም፣ ሕገ መንግሥቱን ለመናድ አስባችኋል በማለት ለአገር ተቆርቋሪ የሆነውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ እያሰረ፣ እየገረፈ፣ ይገላል:: ለአንባቢ ለማስገንዘብ የምፈልገው የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን ወንጀልና ግብታዊ ሴራ ለመተንተን ሳይሆን ዋና ትኩረቱ ስለብሔር ብሔረሰቦች እስከመገንጠል ተብሎ የተሰጠውን መብት በሚመለከትና ከዚያም አንጻር የክልሎቹን አከፋፈልና አደላደል ኢትዮጵያን ለማዳከምና ወያኔን በስልጣን ላይ ለማቆየት ብቻ የተቀየሰ እንጂ ታሪክን ተከትሎ ሚዛናዊ በሆነ መልክ ድልድል እንዳልተደረገ ወይም ለኢትዮጵያ በጎ አስተዳደር ይበጃታል ተብሎ የታቀደ አለመሆኑን ለማሳየት ነው::

ካለፈው ታሪኩ እንደምንገነዘበው፣ ወያኔ ሁልጊዜ የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት የነበረውን ታሪክ መካድና እውነትን በውሸት መደምሰስ የድርጅቱ ባሕርይና የአስተዳደሩ ቋሚ ዘዴ ነው:: በዚህም ምክንያት የታሪክ ክህደትና ውሸት የኢሐድግ መንግሥ የአስተዳደር ዘርፍ መሆኑን እንድናውቀው ይገባል:: ለዚህም ጥሩ ምሳሌ አቶ መለስ፡ የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት፡ በሚለው በመጽሐፋቸው ላይ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አልነበረችም ማለቱና በአልጀርያውና በኮሚሽኑ ድርድር ውጤት ታላቅ ድል አግኝተናል ብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምስራች ማብሰራቸው በቂ ምስክር ነው:: በዚህም አሳፋሪ አባባል እጠየቅብታለሁ ብሎም ሃፍረትና ፍርሃትም አላደረበትም፡ ምክናያቱም ከወያኔ ፓርቲ በላይ ስልጣን ያለው አካል ባለመኖሩና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትጥቅ ያልተደራጀና ትግሉ በሰላማዊ መንገድ ብቻ መሆኑን ስለሚያውቅ ማንኛውንም ውሸት ተቀባይነት እንዲያገኝ በጠመንጃ ኃይል ለማስከበር ስለሚችል ነው:: በእንደዚህ አይነት ተጽእኖ ውሸትን ረዘም ላለ ጊዜ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሕዝቡ ይለምደዋል ከዚያም ውሸቱ እንደ እውነት ሆኖ ይቀራል፣ ታሪኩን የሚያውቀውም ሕዝብ ሽምግሎ ይሞታል፣ እውነትም እያደር ትረሳለች፣ ወጣቱም ትውልድ ቢሆን ከታሪክ አንጻር ተመራምሮ ለእውነት መከራከር ስለሚያዳግተው በዘመኑ የተነገረውን ውሸት እንደ እውነት መቀበል ይገደዳል:: ከዚያም የኢትዮጵያዊነትን እሴት ከሕዝቡ ህሊና ከፋቀ በኋላ ሐገሪቷን ሶስቱ ድርጅቶች በተስማሙበት መሰረት ሊከፋፍሏትና ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ለማጥፋት እችላለሁ ብሎ ያምናል:: እንዲህ ያለው አስተሳሰብና መርሆ በስውርም ሆነ በይፋ በወያኔ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ እጅግ በጣም የሰረጸና በተግባርም እየተፈጸመ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው::

ይሄንን መርሆ በመከተል ከላይ እንደተቀሰው ወያኔ በስልጣን እርከኑ ላይ ከወጣ (ከተቀመጠ) በኋላ በተግባር ለመፈጸም የፈለገው በጫካ በትግል ላይ በነበረበት ዘመን ኢትዮጵያን ለመበታተንና ታላቋን ትግራይ ሪፓብሊክን ለመመስረት "የተሰኔ ማኒፌስቶ" የተባለውን የሴራ እቅድ በሥራ ላይ ማዋል ተቀዳሚ ተግባሩ ነበረ:: የዚህም ሴራ አቀንቃኞች ሻቢያ፣ኦነግና ወያኔ ሲሆኑ፣ የማኒፌስቶውም ዋና አላማ ኤርትራን ከእናት ሐገሯ ማስገንጠል፣ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንድትሆን፣ ኢትዮጵያ የሚለውም ስም እንዲጠፋ በብሔሮች እንድትከፋፈል ነበር:: በስምምነቱም መሰረት ወያኔ በሰኔ ወር 1983 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን አዳራሽ በተሰበሰቡ የሕዝብ ውክልና በሌላቸው ሰዎች "የተሰኔ ማኒፌስቶ" ስምምነት "በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ቻርተር" ላይ እንዲሰፍርና እንዲጸድቅ ተደርጓል::(ሥልጣንተሻሚ ትግሬዎችና የኢትዮጵያ አንድነት-ተክሌ የሻው)

ሻቢያና ወያኔ በትግላቸው ዘመን የሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለም ተከታይ ኢሕአፓና መኢሶን የመሳሰለትን በአንድ ክበብ ውስጥ በማስገባት ለትግላቸው በብዙ መንገድ እንዲያግዙአቸው ተጠቅመውባቸዋል:: ወያኔ በተለይ የትግራይን ልጆች በጦር ሜዳ በማሰልፍ ለኤርትራ ነጻነት ሕይወታቸውንእንዲሰውና እስከ መጨረሻው ነጻነቷን እስከምትቀዳጅ ድረስ እንደታገሉ አድርገዋል:: ይህንንም መስዋትነት የከፈሉ መሆናቸውንና እንዲሁም ወደፊት ነጻነቷን የሚደፍር ወይም የሚቀናቀን ካለ ወይም ጠላት ሊያጠቃት ቢሞክር፣ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር መስዋዕት የሚከፍል መሆኑን ለኤርትራ ሕዝ

ብ ቃል የገቡ መሆናቸውን አቶ ስብሃት ነጋ (አቦይ ስብሃት) ፡ በተለያዩ የዜና ማሠራጫዎች በይፋ አ ረጋግጠዋል። ስለዚህ ወደፊት ከኤርትራ የወደብም ሆነ የድንበር ጥያቄ ለሚያነሱ የጎረቤት ሐገሮች ይሄንን ማስፈራያሪያና ማስጠንቀቂያ መገንዘብ ይኖርባቸዋል ማለት ነው። ኢትዮጵያ የኤርትራን መገንጠል ስለምትቃወም፣ በተለይ የወደብ ጥያቄ ማንሳቷ አይቀርም ተብሎ ስለሚታመን በአንደኛ ደረጃ ጠላትነት የምትፈረጅ መሆኗ አያጠራጥርም።

የብሔር ብሔረሰብ መብት መከበር አለበት በሚል ሳቢያ ወያኔ ያረቀቀው ሕገ መንግሥት በ መሰረቱ ከኮሚኒስት ርዕዮተዓለም የተቀዳ ቢመስልም፣ በጣም ስድና መረን የለቀቀ በመሆኑ የኢትዮ ጵያን አንድነት ለመናድ፣ የታቀደ እንጂ ለብሔሮችም ሆነ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር ታስቦ የተደረገ አለመሆኑ እሙን ነው። በአንቀጽ 39 እንደተጠቀሰው "ማንኛውም የኢትዮ ጵያ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማና ቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው" የሚል ለኢትዮጵያ አንድነት አደገኛ የሆነ አፍራሽ መብ ት ለብሔሮች ብሐረሰቦች ሕዝቦች መስጠቱ አፍራሽ እንጂ ገንቢ እንዳልሆ ለማንም ግልጽ ነው። የ ጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ እንደ የኦሮምና ኦጋዴን ብሔረሰቦችያሉ የኤርትራን ፈለግ ተከትለው ለመገን ጠል የሚያግዳቸው ምንም ዓይነት ሕጋዊ ገደብ የለም።

እርግጥ የኮሚኒስቱ ርዕዮተ ዓለምና የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ለብሔሮችና ሕዝቦ ች "የሰልፍ ዲተርሚኔሽን" መብት ያስፈልጋቸዋል ብለው ያምናሉ። ሆኖም ያሉበት ሁኔታ ሲያስገ ድዳቸውና ምክንያታቸው አጥጋቢ ሆኖ ሲገኝ ነው እንጂ አንድ ብሔረ ሰብ ለስልጣንና ለተወሰነ ብ ሔረሰብ የኢኮኖሚ ግንባታ ለም አገር ከፍሎ ለመውሰድ የሚጠቀምበት መብት አይደለም። ይሄን በ ሚመለከት የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባርና የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር መጥቀሱ ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ለሁሉም ነገር "የሰልፍ ዲተርሚኔሽን" የሚለውን መርሆ መንፈሱንና ምንጬን ከምን እንደመጣ በ ጥቂቱም ቢሆን መተንተኑና መመርመሩ፣ እንዲሁም ይህ መርሆ ጥንታዊትና አህዳዊ የመንግሥት አስተዳደር የነበራት ኢትዮጵያን በመሰለ ሐገር ላይ ሊፈጸምባት ይገባል ወይ? የሚለውን ጥያቄ መ መለስ ያስፈልጋል። የዚህ ርዕዮተ ዓለም፣ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ከላይ እንደተቀሰው ሁለት ምን ጮች አሉት፣ እነሱም የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርና የሶቪየት ዩኒየን ኮሚኒስት መርሆ ናቸው። በመሰረቱ የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የሚለው "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን" ብቻ ነው እንጂ "እስ ከ መገንጠል" የሚለውን ቃል አይጨምርም፣ ይሄውም፣

> "To develop friendly relations among nations based on respect for the principle of equal rights and self determination of peoples, and to take other appropriate measures to strengthen universal peace."

የዚህ አንቀጽ ሕጋዊ ትርጉም ምንም እንኳ ብዙ ቢያከራክርም የጽንሰ ሀሣቡ መነሻ የነበረው በዘመ ኑ ኃያላን መግሥታት አንድ አገር የነበረውን ለሁለት ተካፍለው ሲገዙ ከኖሩ በኋላ ነጻነት በሚያገኙ በት ጊዜ በተለያየ ቅኝ ገዢዎች በመገዛታቸው ምክንያት የተለያየ ባሕልና የቋንቋ ልዩነት ስላካበቱ ወደ ዱሮው አንድነታቸው ለመመለስ ችግር ስለገጠማቸው፣ ውህደቱ በሕዝቡ ፈቃድ እንጂ በግድ እንዳይሆን ሲባል ልል የሆነ አንቀጽ ተጠቀሰላቸው። ለዚህም ጋናና ቤኒን ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ሆ ኖም በሂደት በፈቃደኝነት በቋንቋቸውና በባሕላቸው ለመግባባት ከቻሉ በውህደቱ እንዲስማሙ ካ ልተቻለ ደግሞ መብታቸው ተጠብቆ እራሳቸው እንዲወስኑ ከላይ የተጠቀሰው "ሴልፍ ዲተርሚኔሽ" የሚለው መብት ተሰጣቸው። እንዲሁም ቻርተሩ በተረቀቀበት ዘመን ብዙ የአፍሪካ ሐገሮች በኮለ ኒያሊዝም ግዛት ስር ስለነበሩ ነጻነታቸውን አግኝተው በራሳቸው ፈቃድና ውሳኔ እራሳቸውን ችለ ው እንዲተዳደሩና ኃያላን መንግሥታት ጣልቃ እንዳይገቡ ሰብአዊ መብታቸው እንዳይደፈር የሚ

ከላከል አንቀጽ ነው:: ይህን በሚመለከት የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተለውን ትዕ ዛዝ ለሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅት ሰጥቷል "In its resolution 59/180, the General Assembly requested the Commission on Human Rights to continue to give special attention to the violation of human rights, especially the right to self-determination, resulting from foreign military intervention, aggression or occupation and requested the Secretary-General to report on this question to theAssembly…")
በጥቅሉ ይህ የሚያመለክተው የሰብአዊ መብት እንዲከበርና ኃያላን መንግሥታት ሌሎቹን አናሳ መንግሥታት እንዳይደፍሩ የሚከላከል አንቀጽ ነው::

ስለዚህ ይህ የተባበሩት መንግሥታት የሰጠው መብት፣ በማናቸውም መለኪያ፣ ኢትዮጵያን በመሰለ ጥንታዊና ሉዐላዊ የሆነች አገር እንድትከፋፈል ወይም አንድነቷን ለማፍረስ ተብሎ የተሰጠ መብት አይደለም:: የተባበሩት መንግሥታት ህብረትን ማጎልመስ እንጂ አንድ ሉዐላዊ የሆነ አገር እንድትከፋፈል አይደግፍም፣ ሕግም አይደነግግም:: የተባብሩት መንግሥታት በአንድ ሉአላዊ መን ግሥት ውስጣዊ አስተዳደር ውስጥ በምንም መልኩ ጣልቃ አይገባም:: የግል ነፃነትና ሰብአዊ መብት እንዲከበር ዋና አላማው ነው፣ እንዲሁም አንዱ መንግሥት የሌላውን ሉዐላዊነት እንዳይደፍርና በ ሰላም ተከባብረው ነፃነታቸው ተጠብቆ በእኩልነት እንዲኖሩ መሰረታዊ አላማው ነው:: ስለዚህ በተባ በሩት መንግሥታት ቻርተር "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን" የሚለው አንቀጽ በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፣ አግባብም አይደለም::

እንደምናስታውሰው ከ1960 ዘመን ጀምሮ ጥቂት ድርጅቶች፣ እንደ ኢሕአፓ፣ መኢሶን እን ዲሁም ሌሎች ተራማጅ ድርጅቶችና ግለሰቦች የኮሚኒስት ርዕዮተዓለም በመከተል፣ "ሴልፍ ዲተር ሚኔሽን አፕቱ ሴሴሽን" በማለት በየዋህነትም ሆነ በግብዝነት ዘመኑ ያመጣውን መርሆ እንደፋሽን አንግበው፣ መሬት ላራሹ ለሚለው መሰረታዊ የሕዝብ ጥያቄ፣ የሚያገለግል መስሎአቸው የፖለቲካ ትግል ያካሂዱ ነበር፣ እንዲሁም በአንጻሩ ደግሞ ወያኔና ሻቢያ ኤርትራን ለማስገንጠል አጋር እንዲ ሆኗቸው የሌሎቹ ብሔሮች መብት እንዲከበር በመቀስቀስና በጎሳ በማደራጀት የኢትዮጵያን አንድ ነቷን ለመከፋፈል እየተጠቀሙበት ነበር::

በመጀምሪያ ደረጃ የኮሚኒስቱ የእስታሊን "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን አፕቱ ሴሴሽን" የሚለው መርሆ ጥንታዊት በሆነች ኢትዮጵያን በመሰለ አገር ላይ አግባብ አለው ወይ? የሚለውን ነጥብ በጥ ቂቱም ቢሆን መመርመሩ አስፈላጊ ይመስለኛል:: ይኀንንንም ለማለት ያስቻለኝ ቀደም ብዬ እንደ ጠቀስኩት ምሑሩና ተራማጅ ተማሪው እንዲሁም የግራ ርእዮተ-ዓለም ተከታይ የሆኑ ድርጅቶች ለ ኢትዮጵያ ይበጃታል ብለው ከሶቪየት ዩኒየን፣ ከቻይና፣ ከአልባኒያ ሐገሮች የኮሚኒስት መርሆ እንዳ ለ ጥሬውን ገልብጠው የፖለቲካ ትግል ሲያካሂዱ ስለነበረና የአሁኑም መንግሥት ቢሆን፣ ዲሞክራሲ ን ለይስሙላ ወይም ከለላ እንዲሆነው እንጂ፣ በመሰረቱ በሐገሪቷ የሰፈነው ስርአት የኮሚኒስት መር ሆ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ነው::"ሴልፍ ዲተርሚኔሽን አፕቱ ሴሴችን" የሚለው የኮሚኒስት መርሆ ብ ዙ ሊቃውንቶች የተከራከሩበትና ልዩ ልዩ ትርጉም የሰጡበት እንደመሆኑ መጠን ወደዚህ ትንታኔ ውስጥ አልገባም:: ሆኖም ይሄንን ስርአት በሕገ መንግሥቱ አርቅቆ በስራ ላይ ያዋለ የቀድሞው ሶቪ የት ዩኒየን ስለሆነ፣ የዚህን አገር ሁኔታና እንዲሁም ከላይ የተጠቀሰውን የኮሚኒስት መርሆ ለመጠቀ ም ያስገደዳቸው ወይም ያሳሰባቸው ምክንያቶች መመርመሩ ጠቃሚ ነው::

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1922 በተደረገው አንደኛ ስብሰባ ተብሎ በተጠራው ስብሰባ ላይ አራት ሐገሮች ለመዋሀድ ተስማምተው "ሶቪየት ዩኒየን" የሚለውን አገር ፈጠሩ፣ እነኚህም አገሮ

ች ረሺያ፣ትራንስኮካሲያን፣ ዩክሬን፣ባይሎሩሲያን ነበሩ (RSFSR (Russia), the Transcaucasian SFSR, the UkrainianSSR and |the Byelorussian SSR) ናቸው

• ከጊዜ በሀኋላ ሌሎች እንደነዚሁ እራሳቸውን የቻሉ አገሮች ስለተዋዋሀዱ በጠቅላላው የሶቪየት ዩኒየን አባል አገሮች እስከ አስራ አምስት (15 አገሮች) ደርሰው ነበር:: የውህደቱም ምክንያት ብዙ መልክ ነበረው፣ይህም በስምምነት፣ በፖለቲካ ተጽእኖ፣ የሩሲያን መንግሥት በመፍራት፣እንዲሁም የኮሚኒዝም ርዕዮተዓለም እምነት በመከተል ነበር::

እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት ሐገሮች ከመዋህዳቸው በፊት የየግላቸው ታሪካዊ ዳር ድንበርና እንዲሁም እንደ አንድ ሉአላዊ አገር እውቅና የነበራቸው ነበሩ:: ስለዚህ በአንድነት ከሌሎቹ አገር ጋር በውህደት ተስማምተው ለመኖር ካልቻሉ ወደጥንቱ ታሪካዊ አገርነታቸው ለመመለስ እንዲችሉ ሲባል የኮሚኒስቱ መርሆ "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን አፕቱ ሴሴችን" የሚለው በሥራ ላይ እንዲውል ተስማሙ:: በዚህም ምክንያት በ1991 ዓ.ም የሶቪየት ሕብረት ሲፈርስ እያንዳንዱ አገር የጥንቱ ታሪካዊ ድንበሩ ተከብሮለት ከውህደቱ ተገንጥሎ እራሱን ችሎ ነጻነቱን አውጆ ተከብሮ ይኖራል:: የድንበርም ጭቅጭቅና ጥል አልተሰማም:: ስለዚህ "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን አፕቱ ሴሴሽን"የሚለው መርሆ በቀድሞው የሶቪየት ሕብረት ላይ መዋሉ አግባብ ሊኖረው ይችላል:: የኢትዮጵያ ሁኔታ ግን ከየሶቪየት ሕብረት ሁኔታ ጋር በጣም የተለየ ነው:: ኢትዮጵያ የብዙ ዘመን ነፃነትና አሐዳዊ መንግሥት የነበራት ስለነበረች፣ "ሴልፍ ዲተርሚኔሽን አፕቱ ሴሴችን" የሚለው የኮሚኒስቱ መርሆ፣ እንዲሁም "ሰልፍ ዲተርሚኔሽን" የሚለው የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም::

ከላይ ትንሽ ጠቀስ እንዳደረኩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብአዊ መብቱ ተከብሮለት፣ ምንም አይነት የጎሳ ክልል ገደብ ሳይኖርበት ተመሳጥሮ ተፋቅሮና ተጋብቶ በሰላም ይኖር ነበረ:: በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከግራኝ መሐመድ ጋር በተደረገው ጦርነት፣ በተለይ ጦርነቱ በውጪ ኃይል እየታገዘ ስለነበርና የግራኝ ጦር በጠመንጃ የኢትዮጵያ በጦር ውርወራ ስለነበረ ድሉ ለግራኝና ለደጋፊዎቹ ቱርኮች ስለሆነ ስርወ መንግሥቱን በሸዋ መሐል አርጎ የነበረው መንግሥት ወደ ጎንደር መሰደድ ግድ ሆነበት:: የመሐመድ ግራኝ ጦርነት የኢትዮጵያን መንግሥት ኃይል በጣም አዳክሞት ስለነበረ ለማንኛውም ጠላት ምቹ በር ከፈተልት:: ሕዝቡም የሚከላከልለት መንግሥት ስላልነበረና ስላልተደራጀ ኦሮሞ/ጋላ በቀላሉ ሊወረው ቻለ:: በዚህም ምክንያት የገዳን ስርአት በመከተል በቀላሉ ከደቡብ ተነስቶ መሀል ሐገሩን፣ ምዕራቡንና ሰሜኑን ሊወር ቻለ:: ነባር የነበረውን ሕዝብ ተወልዶ ካደገበት ቀዬው አፈናቅሎ ለስደት ከዳረገው በኋላ የኦሮሞው ሕዝብ ለራሱ ሰፊ መሬት ቀምቶ ያዘ፣ ይህን በሚመለከት (ዜናሁ ለጋላ የሚለው የአባ ባሕርይ መጽሐፍና፣ History of The Galla (Oromo) of Ethiopia by Professor Donald N. Levine) መመልከቱ ምን ያህል የጋላ ወረራ ጨካኝና አረመናዊ ድርጊት እንደፈጸመ ለመረዳት ይቻላል::

የገዳን ስርአት በመሰረቱ በተግባር እንዲፈጸም የሚወስኑት በአካባቢው የኦሮሞ ሕዝብ የተመረጡ ሽማግሌዎች ናቸው:: ለምሳሌ ያህል በአንድ ሰፈር ወይም ቀበሌ አንድ ወጣት ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ ሽማግሌዎቹ ተመካክረው ልጁ አንድ ጀብዱ ሥራ ሠርቶ እስካላሳየ ድረስ ጸጉሩን እንዳይላጭ ሚስትም ለማግባት እንደማይችል ይነግሩታል:: ባህሉ የሚያዘውን "የጉዱሩ ዘመቻ" እንዲፈጽም ያዙታል:: የጀብዱውም አይነት ከኦሮሞ ያልሆነ ቤትሰብ ገድሎ ብልቱን ቆርጦ፣ ጀግንነቱን ለሽማግሌዎቹ ካሳየ በኋላ ከላይ የተጠቀሱትን እግዶች ያነሱለታል:: በተጨማሪ የሚቹን ሚስትና ከብቶች ዘርፎ ልጅም ካለው ቀምቶ ለጉዲፈቻ ይወስዳል:: ሴትም ከሆነች አሳድጎ ያገባታል::ስለዚህ የገዳ ስርአት ምንም እንኳን የሽማግሌዎቹ መመረጥና ሀሳባቸውን በመመካከር መወሰናቸው የዲሞ

ክራሲ መልክ ቢሰጥም የባህሉ ስርአት አረመናዊና ወንጀለኛ ተግባር የሚፈጽም ነው። ከላይ የተጠቀ
ሱት መጻሕፍቶች እንዲህ ያለውን ድርጊትና ሌላውንም አረመናዊ ድርጊታቸውን በዝርዝር ከመግለ
ጻቸውም በላይ የወረሯቸውን ክፍለ ሐገሮችና በግድ ያስለቀቋቸውን ነገዶችና ጎሳዎች ጭምር ያስረ
ዱናል። ሸዋን፤ አሩሲን፤ ሐረርጌ፤ ባሌ፤ ከፋን፤ ወሎን፤ ወለጋን፤ የደቡብን ሐገር ሕዝብ እንዲሁም ሌ
ሎቹን ክፍለ ሐገሮች በመውረርና ነባሩን ሕዝብ በማፈናቀል ለራሳቸው ተስፋፍውተው መሬት ሰፊ
መሬት እንደያዙ ያስረዳናል።

ሆኖም ይሄንን ወረራ ድል አድርገው ስርአትና ጸትታን አረጋግተው ያስተዳድሩ የነበሩት የ
ዘመኑ ነገሥታት እንዲሁም ተከታዮቻቸው የኦሮሞን ሕዝብ በጦር ኃይል በግድ የያዘውን ለማስለቀ
ቅ ሲችሉ ተባብረው አብሮ መኖርን መረጡ እንጂ ወራሪ ነህ ብለው አላስወጧቸውም። የኦሮሞ ሕዝ
ብም የዘላን ኑሮውን በመተው እንደሌላው ኢትዮጵያዊ፤ እንደ ዐማራና ትግሬ ቤት ሰርቶና መሬት
ይዞ እያረሰ መኖር ጀመረ። ከዚያም በመንግሥት አቋማት ሁሉ በብዙ ዘርፍ እየተካፈለ ለኢትዮጵያ
እድገትና ስልጣኔ ታላቅ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ኖሯል። በእስካሁን ቆይታው በኢትዮጵያዊነቱ ከሌለ
ቹ ኢትዮጵያዊ ጋር ተመሳጥሮ በየክፍለ ሐገሩ ይኖር ነበረ እንጂ በጎሳነቱና በቋንቋው ልዩነት ምክን
ያት የኦሮሞ አገር ተብሎ የተሰጠው የራሱ የሆነ ታሪካዊ ክልል አልነበረውም።

ወያኔ እንዲህ ያለውን ታሪካዊ ሐቅ ሊቀበለው አይፈልግም፤ ምክንያቱም ዋንው ትኩረቱ አ
ማራውን በመወንጀልና ኢትዮጵያን ለመበታተን ስለሆነ የብሔሮችን በተለይ የትግራይ ሕዝብ ጭቆ
ና በአማራው ብሔረሰብ ጨቋኝነት ምክንያት ነው ብሎ ሕብረተሰቡን በውሸት ለማሳመን ስለሚፈ
ልግ ነው። በዚህም ምክንያት በትግራይ ሕዝብ ላይ የደረሰው የድርቅ ሰቆቃ በጨቋኙ ዐማራ ብሔረ
ሰብ አገዛዝ ምክንያት ነው በማለት የትግሬ ተወላጅ ሁሉ በአማራው ብሔረሰብ ላይ እንዲነሳ በመቀ
ስቀስ በሕዝቡ መሀል ጥላቻ እንዲፈጠር አድርጓል፤ እንዲሁም ሌሎቹን ብሔረሰብ በአማራው ላይ
ጥላቻ እንዲያድርባቸውና ከየክልሉ አማራው እንዲባረርና እንዲገደለም ቅስቀሳ አድርጓል። የራሱን
ም ሕዝብ በሚከተለው የግጥም መፈክር ቅስቀሳ አድርጓል፤

" ጎበዝ ተሓሕት ተጋዳላይ ትግራይ
አርኪብካ በሎ ንዚ -ሃሻ-አምሃራይ

ትርጉም፤

" ጎበዝ ድል አድርግ የትግራይ ተጋዳይ
ተከትለህ በለው ይህን ውሻ አማራ፤"

( ተክሌ በሻህ ገ.350)

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ አማራውን ተከታትለህ በለው ሲል በሌላ በኩል የሌላውን ጎሳ ሕዝ
ብ በብሔር እያደራጀ በአማራው ላይ እንዲነሱ በውሸት የተመረዘ ፕሮፓጋንዳ ይነዛል። አማራው የ
አገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ጭብጠውን ሰንቆ ከጠረፍ ጠረፍ እየተንከራተተ ከጠላት ጋር እየተዋ
ደቀ ደሙንና ሕይውቱን ሲሰዋ የኖረበትን ዘመን፤ ለኢትዮጵያ ሐገሩ ብሔራዊ ግዴታውን የከፈለበ
ት አገልግሎት ወሮታ መሆን ሲገባው፤ ወያኔ ነፍጠኛ ጨቋኝ በሚል ዕቡይ አስተሳሰብ ሌሎች ብሔ
ሮች እንዲኮንኑት በኢኮኖሚውና በሕይወቱ ላይ አደጋ እንዲጥሉበት በተግባር አሳይቷል። በአርሲ፤
በአርባጉጉ፤ በሐረር፤ በጎንደር፤ በወለጋ፤ በቤንሻንጉል በአማራው ላይ የተፈጸመው የነፍስ ግድያ ለ
ማይሙና ያህል ጠቀስነው እንጂ በአማራው ላይ የደረሰው አረመኔያዊ ግድያ እጅግ በጣም አሰቃቂ
ነው። ወያኔ ወደፊት ለሚፈጥራት የትግራይ ሪፑብሊክ ነጻነቷን ተቀናጅታና ሰኩሪቲዋ ቀጣይነት
እንዲኖረው በማሰብ፤ በተለይ አማራው ተቀናቃኝ ነው ብለው ስለሚያምኑ በትምህርት እንዲደነ
ቁርና በኢኮኖሚውም እንዲደኅይ በክልሉ ለማይሙና ያህል እንጂ እዚህ ግባ የሚሉት የኢኮኖሚ ግ

ንባታ የለም። እንዲሁም የብሔሮች መብት ይጠበቅ በሚል ሽፋን የሚናገሩት ቋንቋ ትግርሪኛ ወይም ኦሮምኛ ነው በማለት ከአራቱም ማዕዘን ነጥቆ ለሌሎች ብሔሮች ሰጥቷል። በመሰረቱ ክልሎች በቋንቋ መከፋፈል ካለባቸው አማርኛ ተናጋሪው በጣም ብዛት ያለውና በብዙ ቦታ የሰፈረ ስለሆነ የአማራው ክልል ከአሁኑ ይዞታው በጥቂቱ ሶስት እጥፍ መሆን ነበረበት።

ክልሎቹ የተሸነሸኑት ሕዝቡ ተስማምቶበት ሳይሆን፣ ሁለቱ ድርጅቶች፣ ወያኔና ኦነግ በተስማሙበት መሰረት ነው። በዚህም ምክንያት ወያኔ ከጎንደር ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ የሡቲትና የጠለምትን ወረዳዎች፣ ሁመራን እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች ወስዷል፣ ከወሎ ማይጨውን፣ ሰቆጣን፣ ወልድያን እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች ወስዷል። ኦነግም ግማሽ ሸዋን፣ አሩሲን፣ ሐረርን ባሌን፣ ወለጋን፣ እንዲሁም ከደቡብ ሐገሮች ወደ ክልሉ አጠቃሏል። በተለይ ከግማሽ በላይ የሸዋ ክፍለ ሐገር ለኦሮሞ ሕዝብ እንዲሰጥ የተደረገበት ምክንያት ወያኔ በዚህ ክፍለ ሐገር ባለው የአማራ ብሔርሰብ ላይ የከረረ ጥላቻ ያለው በመሆኑ የበቀል መወጫ እንደሆነ የታመነ ነው። ይሄም አማራው በድንቁርናና በድህነት ተሽመድምዶ ወደፊት እንኳንስ ለኢትዮጵያ አንድነት ሊታገል ይቅርና የራሱን ሕልውና እንኳን ለማስከበር የማይችልበት ደረጃ እንዲደርስ የታቀደ ደባ ነው። ዋናው የወያኔ ዕቅድ የአማራውን ብሔር መጀመሪያ ለማዳከምና ከዚያም ኢትዮጵያን እሱ በመረጠው አይነትና ጊዜ ከፋፍሎ አንድነቷን ለማጥፋት ነው። አቶ መለስ ዜናዊ "የኤርትራ ትግል ከየት እስከየት" በሚለው መጽሐፋቸው ስለአማራውና ስለ ኢትዮጵያ ሲያትቱ

> "ገና ድሮ ጀምሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ነብረች በማለት የአማራው ብሔር የገዢ መደቦችና ቡችላ የሆኑት የታሪክ ጸሐፊዎቻቸው፣ በታሪክ ስም የሚያቀርቡትንና የሚዘረጉትን አፈታሪክ ቁጥሩ የማይናቅ ሕዝብ እንደትክክለኛ ሐቀኛ አድርጎና ተመልክቶ ይቀበለዋል። ዳሩ ግን ይህ ከአንድ አፈታሪክ በምንም ዓይነት መንገድ የማይለይ ፍጹም ሀሰት ላይ የተመሰረተ አባባል ነው።" (ተክሌ በሻህ 357-58) ከዚያም በመቀጠል "ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች አንድ አገር መሆን የጀመረችው በአክሱም ዘመነ መንግሥት ሥልጣኔ ወቅት አይደልም፡ የአክሱም መንግስትም የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ግዛቶች በሙሉ ያጠቃለለ እንዳልነበር ታሪክ በማያውላውል መንገድ አስቀምጦታል። የምኒልክ ንግሥና እስኪመሰረት ድረስም ቢሆን ዛሬ ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራትን በአንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ስር በማድረግ የሚመራ መንግሥት አልነበረም"(ተክሌ በሻህ 359

ከነኚህ ሁለቱ አተታዎች የምንገነዘበው ወያኔ የኢትዮጵያን ጥንታዊነት የማያምንና እንዲሁም አማራው ስለኢትዮጵያ ጥንታዊነትና አህዳዊነት የሚናገረውና የሚጽፈው አፈታሪክ እንጂ እውነኛ ታሪክ ነው ብሎ አያምንም። ከላይ እንደጠቀስኩት ሁሉ ወያኔ በኢትዮጵያና በአማራው ላይ ያደረሰው ወንጀልና ጥቃት ብዙ አሰቃቂ ታሪክ ስላለው፣ ያን ሁሉ በዚህ አጭር ጽሁፍ ለመዘርዘር አይቻልም፣ ሆኖም ከሚናገረውና በተግባር ከሚፈጽመው ተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሳት የብሔሮች መብት ይከበር በሚል ሳቢይ የአማራውን ብሔር በወንጀለኛ ፈርጆ ሀብቱን ቀምቶ ህልውናውን ከአጠፋ በኋላ ኢትዮጵያን ለመበታተን እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይኅን በሚመለከት ወያኔ አዲስ አበባ እንደገባ በ1983 በሰኔ ወር በተደረገው ጉባኤ ደርግን ጨምሮ ወደ ኋላ የነበሩት መንግሥታት ዘመን ለደረሰው ስህተትም ሆነ ጥፋት ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ኋላቀርነትም ሆነ የሕዝቡ ድህነት ሊከሰት የቻለው በአማራው ጨቋኝነት ምክንያት ነው ተብሎ ስለተፈረደበት በኮንፈረንሱ እንዳይካፈል ታግዷ

ል። በዚህም ምክንያት በስብሰባው በተደረጉት ውሳኔዎች ሁሉ ኤርትራ እንድትገነጠልም ሆነ የኢት ዮጵያ ሕዝብ በቋንቋና በጎሳ እንዲከፋፈል በጸደቀው ቻርተር ላይ አማራው ድምጽ አልሰጠበትም።

አንዱ የስብሰባው አላማ ሌላው ብሔረሰብ በአማራው ላይ ጥላቻና ቂምበቀል እንዲያድርበት ስለነበረ፤ ምንም ጊዜ ሳይወስድባቸው ጥቂት ብሔሮች እንደ ኦሮሞ፤ ሱማሌ፡ ቤንሻንጉል የመሳሰሉ ት የአማራውን ጎሳ ከየክልላቸው ውጡልን በማለት በአርሲ፤ በአርባ ጉጉ፤ በአሰቦ ደብር፤ በሐረር፤ በ ኡጋዴን፤ በቤንሻንጉል፤ በአሶሳ፤ በወለጋ፤ እንዲሁም በምሥራቅ ሸዋ በመጨፍጨፍ፡ በመግደል፡ ቤቱ ን በማቃጠል ተወልዶ ካደገበት ቀዬው በማፈናቀል በስቃይ አባረውታል። እነኚህ ድርጊቶች አሁን ም ቢሆን እያሰለሱ በመከሰት ላይ ናቸው።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ወያኔ ሕገመንግሥቱን ያረቀቀውና አገሪቷን በቋንቋና በጎሳ ሸንሽኖ በክልል የከፋፈላት "በተሰኔ ማኒፌስቶ" በተባለው የሴራ ዕቅድ መሠረት ኢትዮጵያን ለመበታተና አንድነቷን ለማፍረስ ስለፈለገ ነው እንጂ ለኢትዮጵያ እድገትና ደህንነት የታሰበ አለመ ሆኑ እሙን መሆኑን ለማሳየት ነው። ይኅንንም በሥራ ላይ ለማዋል እንቅፋት እንዳይሆንበት የአማ ራውን ብሔረሰብ በኢኮኖሚው፤ በትምህርት፤ በፖለቲካ ተሳትፎ፤ በመሬት ይዞታው እንዲሁም በሌ ላውም ዘርፍ እንዳይካፈልና በሂደት ተዳክሞ እንኳንስ ለኢትዮጵያ አንድነት ሊከራከር ይቅርና ለራ ሱ መብት እንኳን ለመናገር የማይችልበት ደረጃ እንዲደርስ የታቀደ ሴራ ነው። የወያኔ አላማ ገና ከ መጀመሪያ ሲያቅዱ እንዲሁም አሁን በሂደት በተግባር ላይ የሚታየው፤ ኢትዮጵያን ለማጥፋት መ ሆኑ እሙን ነው፤ አሁን ያለው ሕገመንግሥትና በብሔሮች መብት ሽፋን የተከለሉት ክፍለ ሐገሮች ኢትዮጵያን ለመበታተን ከታቀደው ስራት አንዱ ዘርፍ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ አንድነት እንዲከበርና እንዲሁም ሕዝቡ በጎሳና በቋንቋ ሳይከፋፈል በሰላ ምና በወንድማምችነት እንዲኖር ከተፈለገ ወደ 1966 የአስተዳደር ክልል መመለሱ እጅግ ተመራ ጭ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ክፍለ ሐገር የብዙ ብሐሮች ወይም የሕብረ ብሔሮች ተወልደውና አድገው የሚኖሩበት መዲናቸው እንደመሆኑ መጠን በክልል ድንበር ሳቢይ የኔ ነው በማለት ከሌላ ው ጎሳ ጋር በድንበር የመጋጨት አስተሳሰብና ምክንያት አይኖራቸውም፤ ከተፈለገም ደግሞ 1966 የነበሩትን ክፍለ ሐገሮች በፌዴራል መልክ ለአስተዳደርና ለታክስ ስብሰባ ምቹ እንዲሆን ዘርን ሳይ መለከት ለማዋቀር ይቻላል። ከላይ ለመተንተን እንደተሞከረው ኢዮትጵያ ከጥንት ጀምሮ አህዳዊ አ ካልና በአህዳዊ መንግሥት ስትተዳደር ስለነበረ እያንዳንዱ ጎሳ ታሪካዊ ክልልና ድንበር ስላልነበረው ፤ ያልነብረውንና የሌለውን ክፍለ ሐገር ወስዶ ከተመቸው በኢትዮጵያ ሉአላዊ ስር ለመኖር ካልተመ ቸው ደግሞ ለመገንጠል የሚያስችል መብት ሊኖረው አይገባም።

አባቶቻችን ለኢትዮጵያ ነጻነትና አንድነት ደማቸውን በማፍሰስ አጥንታቸውን በመከስከስ ላለፉ ት ዘመናት በየጦር ሜዳው እየተዋደቁ ውድ ሕይውታቸውን ሰውተው ለኛ ሲያስረክቡን እኛም በ ጋራ ተፋቅረንና ተስማምተን አንድነቷን ጠብቀን ሉአላዊነቷን አስከብረን በሰላምና በጸጋ እንድንኖር እንጂ ወያኔ የተለመውን ዕቡይ ስርአት ተከትለን እንድንበታትናት አይደለም።ኢትይዮጵያ የሁላች ንም ናት ማንኛውም ጎሳ ወይም ዜጋ ከኢትዮጵያ መልከአ ምድር አካል ቆርሶ ወይም ከፍሎ የግሌ ነ ው ሊል አይችልም። አባቶቻችን ያወረሱን መላው አካሏን ለመላው ኢትዮጵያኖች ነው። ሁላችንም የኢትዮጵያ ሉአላዊ ዜግነት ያለን ሁሉ በየትኛውም ክፍለ ሐገር ወይም ክልል የመኖር፤ የመጠቀም፤ የመደሰት መብት አለን። በዚያው አንጻር ደግሞ ሐገሪቷን ከጠላት አጥቂና ወራሪ የመከላከል አን ድነቷን የመጠበቅና ሉአላዊነቷን የማስከበር ግዴታ አለበን። አሁን የምንከተለው የቂም በቀል መሰሪ ስርአት ለማነኛችንም ኢትዮጵያኖች አይጠቅመንም። አፍራሽ እንጂ ገንቢ አይደለም።

ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው በሰላምና በጸጋ፣ በፍቅርና በብልጽግና፣ እንድንኖር ከተፈለገ ወደ1966 ወደነበረው ክልላችን መመለስ ይኖርብናል። ይኅን ሀሳብ አንቀበልም ካልንና ወያኔ በተለ መው ሕገመንንግሥት መሰረት በጎሳና በቋንቋ የብሔሮች መብት መከበር አለበት በሚል ሳቢያ የክ ልል መንግሥታት መመስረት አለበት ከተባለ ደግሞ ወደ ጥንቱ ታሪካዊ ድንበራችን ከግራኝና ከኦሮ ሞ ወረራ በፊት ወዳለው ይዞታችን መመለስ ይኖርብናል። ምክንያቱም አማራው፣ ጉራጌው፣ ሐዲያ ው፣ የደቡብ ሕዝብ፣ እንዲሁም ሌሎች ብሔሮች በግራኝና በኦሮሞ ወረራ በአረመኔ ድርጊትና በግፍ የነበራቸውን ይዞታ ስለተነጠቁ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእነኚህ ሁለት አማራጭ ሃሳቦች ልዩትኩ ረት ሰጥቶ የኢትዮጵያ አንድነቷ የሚጠበቅበትን ሉአላዊነቷ የሚከበርበትንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተ ለይ መጪው ትውልድ በሰላም የሚኖርበትን ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት።